

የደራሲ ፀሐይ መላኩ ‘‘ቁሳ’’ ከለንባብያን እጅ የገባችው ፤ የሴት እህቶቻችን የፈጠራ ብዕር ለምን ድፍረት ለጣ ? እያልን በም ንጠይቅበትና በምንወያይበት ወቅት ነው።

ደራሲዋ በዚህን መስሉ አጋጣሚ ነው ‘‘እነሆ’’ ብላ የብዕር ጭማቂ የያዘውን እጇዋን የዘረጋችልን ።

የያታን ተጽዕኖ የብረት አጥር ጥሳ የወጣችው ‘‘ቁሳ’’ የተጻ ፈነን የፍቅርና የበቀል ቁርሾ ገላልጣ የምታስነብብ ክሽን ያለች መጽ ሐፍ ነች ።

የደራሲዋ የቃላት አጠቃቀምና የአገላለጽ ብርታት ለወፊደቱ የተሻሉ ሥራዎቿም ማረጋገጫ እንዲሆን የጅምሩ መንደርደሪያ ምስ ክር ነው ።

ዳግላስ ጴጥሮስ

Metropolitan Toronto Reference Library
1 6048 3002 2890 2

ዋጋው 5.50

ከ ፀሐይ መላኩ

AMH
892.87
S113
LANG&L
OPENCI

Qwasa : leb walad / ka
Sahay Malaku.
Sahay Malaku.

1300228902
OpenShlf-CR FLOOR 5

A240
X 37
ET6764LP
.484
QWASA. LEB WALAD

ቋሳ

ልብ ወለድ

ከ

ፀሐይ መላኩ

1982 ዓ. ም.

አዲስ አበባ

የደራሲዋ መብት በሕግ
የተጠበቀ ነው ።

ማውጫ

	ገጽ
ምዕራፍ አንድ	7
ምዕራፍ ሁለት	56
ምዕራፍ ሦስት	85
ምዕራፍ አራት	137
ምዕራፍ አምስት	157
ምዕራፍ ስድስት	168
ምዕራፍ ሰባት	180
ምዕራፍ ስምንት	232
ምዕራፍ ዘጠኝ	261

“ . . . የህሊናዬ ቁስል አሁንም ስለሚደማ አክሜ ለማዳን የሙያዬ ብቃት አልረዳኝም ። ደም በደም ይነጻል የሚል እምነት ስላለኝ በዚያ ደም ተለቃልቄ ፈውስ ለማግኘት ምኞትና እቅድ አለኝ ።

ጊዜና ሁኔታ አመቻችተው ለበደል ቢዳርጉኝም ፤ በችግር ጫና ብልጣ ብልጦች ሕይወቴን ቢያወላግዱትም፤ አካሌ እንጂ መንፈሴ በበታችነት አልወደቀምና በሴትነት ተፈጥሮዬ የአበሻነት ኩራቴ ልቤን ሞልቶታል ።

ውርደት እንደሚጠየፉት ጀግኖች በደል እየከረፉኝ እኔነቴ ለበቀል እንዳሸመቀ ፤ ልቤ ያቋተው ቋሳም እንደደረ ነው ። . . . ”

ይህ PDF የቀረበልዎ በ www.binyamhk.wordpress.com ነዉ!!

ምዕራፍ አንድ

ረዥም ቁመናዋ ግዙፍ ሰውነቷና ብሩህ ቀለሟ ተጋግዘው ከሰዎች መካከል በሩቁ እንድትለይ ጉልታ እንድትታይ ያደርጋሉ ። አይኖችዋ ፤ ጉንጮችዋ ፤ አፍንጫዋም ሥጋ የተደራረበባቸው በመሆኑ ፊቷ ያበጠ ቢመስልም የቀዳዋ ጥራት ማማር ይጋርደዋል ። አካሄደ መልካም አለባበስ አዋቂ በመሆኗ ዐይን ያርፍባታል ።

ትክለ ሰውነቷ የአካሄድና የአለባበስ ሥርዓቷ ፤ መልኳ ወይም ጠባይዋ ፤ በሀብትና በቤተዘመድ ብዛት የደረጀው ቤተሰብዋ ፤ ብቻ ፤ አንዱ ወይም ሁሉም ተጠቃለው ማርኪውት ይሆናል ፤ ውብሸት እንዳይላሉ መንፈሱ የሰከነባት ሴት ነች ።

ውብሸት እንዳይላሉ በሎጋ ቁመናው በተዋጣለት መልኩ በዝምታውና በእርጋታው ሳቢያ ሴቶችን ለፍቅር፤ ለሀሳብ ፤ ለናፍቆት ፤ ለንዴትና ለበሽታ የዳረገ መልካም ጐልማሳ ነው ።

በአርባ ሶስተኛው ዕድሜ ዘመኑ ሰክኖ ከአንዲት ሴት ጓደኛው ጋር መዋል መሰንበቱ ዘመዶቹንና ጓደኞቹን የአካባቢውንም ነዋሪ ያስገረመውን ያህል የግቢውን ዘበኛም ድንቅ ይላቸዋል ። “ አለ” “ የለም” እያሉ ብዙ ቆነጃጅትን ማስተናገዳቸው ከተቋረጠ ሰንብቷል ።

ሳብ ረገብ በሚል አካሄድዋ ግዙፍ ሰውነቷን ተሸክማ በአለባበስ አምራ በቅላቷ ደምቃ አጠገባቸው ስትደርስ ዘበኛው በሰላምታ ተቀብለው የውብሽት እንዳይላሉን መኖር ነግረው አሳለፏት ። አብሯቸው የቀረውን የሽቶዋን መዓዛ እያደነቁ ለጥቂት ርቀት አበባየሁን በዐይናቸው ሸኟት ።

የሌሊት ልብሱን እንደለበሰ በእንግዳ መቀበያ ክፍሉ ውስጥ ጋዜጣ ሲያገላብጥ ነበር የደረሰችው ። ልማድ አድርጎት በአገኛት ቁጥር መጀመሪያ አይኖችዋን ፤ ቀጥሎም አፍንጫዋን በኋላም ከናፍርዋን ይስማል ። ያው እንደ ልማዱ ፊቷን ሁሉ ሳመና ከጐኑ ጐትቶ አስቀመጣት ። የሽቶዋ መዓዛ አወደው ። ለጥቂት ደቂቃዎች በጡቶችዋ መሀል አፍንጫውን ሰክቶ ጠረንዋን ማገው ።

ከጡቶችዋ ዝቅ ብሎ ሆድዋን ሊዳብስ ሲቃጣ እጁን ገፋችው ። ቀና ብሎ በፈገግታ ተመለከታት ። እሷም በተፍለቀለቀ ፈገግታ እንደ መሾኮርመም ብላ ለአፍታ አየችው ።

“ ምነው ” አላት ።

“ ምኑ”

“ እጄን ለምን ገፋሽው ”

“ ለሆዴ ጥንቃቄ ማድረግ ፈልጌያለሁ ”

“ ምን ሆነና”

“ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ሆነ ”

“ ምን ተገኘበት ”

“ ቁም ነገር ”

በፌዝ አመለካከት ከገረመማት በኋላ ረዥም ሰውነቱን በፍጥነት ሰብስቦ ተነስቶ ፤

“ በምን ሳስተናግድሽ እመቤቴ ፍላጐትሽን ባውቀው ” አላት

“ ምንም ”

“ ለምን ምንም ”

“ በቃኝ መብላት መጠጣት አስጠልቶኛል ”

“ ዛሬ ከምንጊዜውም የበለጠ አምረሽ ስለተዋብሽ መልኬ በቃኝ ማለትሽ እንዳይሆን ”

“ ለማንኛውም አላሰኘኝም ”

“ ምን ችግር ገጠመሽ እመቤቴ ” አላት አሁንም ፌዝ በሰረጸው አባባል

“ እርግገርስሁ ” አለችው ወደሶፋው እንደመለጠጥ ብላ ።

“ አይደረግም ”

“ ሆኗል ”

ተመልሶ ከአጠገቧ ተቀመጠ ። ለጥቂት ደቂቃዎች በዝምታ ተመለከታት ። እሷም ቃሉን ሲሰማ ሕሊናው የሰጠውን ምላሽ ለማንበብ ተመኝታ ዐይኖቹን ልብ ብላ አስተዋለቻቸው ።

“ ታሾፊያለሽ ” አላት በመገረም ጥያቄ ፡

“ ምን ሹፈት አለ ዕድገት በውስጤ ያንሠራራል ፡

ለውጥ በአካሌም በመንፈሴም ይሰማኛል ። ይልቅ እንዴት ትቀበለዋለህ ”

“ ምኑን ”

“ እርግዝናውን ”

“ ሊገባኝ አልቻለም ”

ከተቀመጠችበት ተስፈንጥራ ተነሣች ። ቅልጥፍናዋ ቀጫጭን ሴቶችን የሚያስንቅ ዓይነት ነበር ። አንጋጠ ከቅምጡ ተመለከታት ።

" ምነው እመቤቴ " አላት ከተቀመጠበት ሳይነሳ

" ቁርጡን ማወቅ እፈልጋለሁ ። ፍረድበት ወይም ፍረድለት "

" በምኑ ላይ ነው ፍረድና ውሣኔው "

በ " በጽንሱ ላይ ነዋ "

" ምን እንዲሆን "

" ሰው ሆኖ እንዲወለድ ወይም ሳይነቃ እንዲቀጭ "

የተዘረጉ ረጃጅም እግሮቹን ሰብስቦ በዝግታ ተነስቶ አልፏት ወደ ተከፈተው መስኮት ሄደ ። ውጭ ውጭውን እያየ እጆቹን በሌሊት ልብሱ ኪስ ውስጥ ከቶ ጀርባውን ሰጥቷት ቆመ ። ወዲያው በሀሳብ ነጉዶ ። " እርግዝለሁ" አባባልዋ በህሊናው ውስጥ መላልሶ አስተጋባ ። ቃሉ የቀሰቀሰው ስሜትና ትዝታ ቀስ በቀስ እየነዳ ባሳለፋቸው የሕይወት ገመናው የዕድሜ መንገዱ ውስጥ የኋሊት ገፈተሩት ።

አበባየሁም ሕሊናዋን ሲያስጨንቀው ለሰነበተው ጉዳይ አንዳችም መልስ በመነፈጓ ሰውነቷ በንዴትና በቁጭት በመጋሉ እንደመንቀጥቀጥ ሲሰማት ተመልሳ ቁጭ አለች ። እሷም ሀሳብ በዝምታ ማባዘት ጀመረች ። ከዚህ ቀደም የገጠሟትን ችግሮችና የመፍትሔ ጥረቶችዋን እንደገና አሰላሰለች ። በዚህ መሰሉ ወቅት ችግሯን የምትቀርፍበትን የገንዘብ አቅሟን በመጀመሪያ ገመተችው ። የባንክ ደብተሯን በዓይነ ሕሊናዋ አገላብጣ ተጽናናችበት። በዚህ መሰሉ ችግር ወቅት የሚተባበራትን ባለሙያ ሰው

አሰበችው ። መልኩ ቁመናው ተግባሩ ታያት ። በመስሪያ ቤቱ ሳይሆን በመኖሪያ ቤቱ በስተጀርባ በልዩ ክፍሉ በተመሣሣይ ችግር የተጠመዱ ሴቶችን ሲያስተናግድ ተመለከተችው ። ማመን መታመን በነጠፈባት ፍቅር ሳቢያ ጠንቅ ላሶው ችግር የተዳረጉ ፡ በተለያየ የኑሮ አቋምና ወግ ተጽዕኖዎች ግፊት ሕይወት ሊቀጩ በጨከኑና ምናልባትም ማስወረድ ወደ መቃብር መውረድ ለሚሆንባቸው ሴቶች ልባዊ አዘኔታ ተሰማት ። የሴቶቹ ዕንባና ጭንቀት ጣዕራቸው ዘገነናት ። እንደገና እሷም ይህን ዕጣ ለመቀበል በመዘጋጀትዋ ዕድልዋን አማረረች ።

ወይዋናው ጉዳይዋ ተመልሳ ንድፍ ማዘጋጀት ጀመረች ። ሥራዋንና የዓመት ፈቃድ ጊዜዋን ፡ አለቃዋንና የፈቃድ አጠያየቁን ስልት ፡ የማስወረጃ ጊዜውንና የሕመሟን ሰሞን እንደየመልኩ ከሚመሳሰል ምክንያት ጋር አጣጥማ ቀረጸችው ። በይበልጥም የጽንሱ ዕድሜ አጭር መሆን ለልብዋ ጥንካሬ ሰጠው ።

የሁለት ወር ጽንስ ማስወገድ ችግር ቢኖረውም ለሕይወት ማጣት እንደማያደርስ ደጋግማ የምታውቀው እውነት በመሆኑ እጅግም አልሰጋችበትም ። ይልቅስ ያሳዘናትና የሰለቻት የወንዶችን ጸባይና ገላ ማሚሸትና ፍቅር ሲጠወልግ ፡ ፍላጐት ሲረግብ መሸኘት ነው ። ይህን ስታወሳ የሕሊናዋ ወቀሳ ወዲያው ጠንክሮ ተጋፈጣት ። " ነፍሰ ገዳይ " " የመቅሰፍት ስለት " ይላት ጀመር ። " ንዝህላል ፡ ሁለተኛውን በአንደኛው ፡ ሶስተኛውን በሁለተኛው ችግር መማር ያልቻልሽ ከቦት" ይላት ጀመር ። ይህ የራሷ በራሷ ወቀሳና ትችት ያሳለፈችውን ስህተትና ችግር እየገላለጠ መጣባት ።

እውነትነት በገሯደላቸው ቃላት ፡ ልባዊነት በሌላቸው በረከቶች ፡ ተንኮል ባሸመቁ የተስፋ እቅዶች ፡ ማስ

መስልና መምሰል በሚችሉ ወንዶች ሽፍጥ የገጠማት ችግር በቀናነትዋ ፥ በአመኔታዋ የተከፈለችው መራራ ምላሽ ትንደሆን ለራሷ በመማል ከሕሊናዋ ሥር መንፈስዋ ስብር ብሎ ሽብረክ እንዳለ አካልዋም እጥፍ ብሎ አጐን ብሳ መሬት መሬቱን አየች ። ሆድ ባሳትና የልቅሶ ስሜት ሲወራት ተነስተሽ ብረሪ አላት ። ደሟ በግለት ተረጨ ።

ጀርባውን ለሷ ሰጥቶ በዝምታ የቆመውን ወዳጅዋን ለአፍታ አስተዋለችው ። ከሁለት ዓመት የፍቅር ቆይታ በኋላ ለረዥም ጊዜ ጀርባውን ሰጥቷት የቆመው ያኔ በመ ሆኑ በትዝብት ከላይ እስከ ታች ቃኘችው ። ሲቃ ተናነቃት ። በውስጧ የሚተራመሰው ሀሳብ ንዴትና ቁጭት ድምጽዋን ስለሰለበው ልትናገረው ፈልጋ ተሳናት ። ለዚህ ችግር የወል ኃላፊነት ያለበት ወዳጅዋ ጀርባውን ስላዞረባት እልህዋን ብሶትዋን በልቅሶ መክፈል ወደምትችልበት የጓደኛዋ ቤት ለመሄድ ወሰነች ። የሕሊናዋንም ወቀሳና ትችት እዚሁ ጥላ ብትሄድ ፈቃድዋ ነበር ። በዚህ ጉዳይ ላይ እንደገና ለማሰብ እንደገና ለመነጋገር ጭራሽ አስጠልቷታል ። ሕሊናዋ ግን የማይገነጠል አካል ነውና በጸጸት እየሸነቆጠ ተከትሏት ሊሄድ መሆኑን አውቃ ከዚህ የራስ ጭቅጭቅ በሽሽት ለማምለጥ የምትችልበትን መንገድ ሁሉ ፈለገች ። ባይፍቀውም ፥ ለተወሰነ ጊዜ የአልኮል ጉልበት እንደሚያደበዝዘው አምና ለዚህም ተዘጋጀች ። ቦርሣዋን አንጠልጥላ አፈፍ ብላ ተነሣች ። ኮቴዋን ሲሰማ ውብሸትም ከሰመጠበት ሃሳብ ተመንጭቆ ወጣ ። ዞረና ከመንገዱ ጐትቶ መለሳት ።

ዐይኖቿ ላይ የተቋጠረው እንባ ቦይ ሰርቶ ወረደ ። እሱ ግን በፈገግታ ከላይ እስከ ታች እንደ አዲስ ሰው ተመለከታት ። ወደ ሰውነቱ ሊያስጠጋት ሲሞክር ገፋችው ። ትክ ብሎ ዐይን ዐይኗን አያት ። በቁመት የማይበላለጡ

ግዙፎች በመሆናቸው እሷም ዐይኖቹን ትኩር አድርጋ ተመለከተቻቸው ። ከአፉ የሚወጣውን የመጨረሻ ቃል ለማዳመጥ እጅግ ተጠንቅቃ ጠበቀችው ። ፈገግታው እየዳመነ ፥ የግንባሩ ቆዳ ቀስ በቀስ እየተሰበሰበ የእጁ ግለት እየጨመረ ፥ አስተያየቱ እየጠነከረ በመምጣቱ የወትሮ ውብሸት እንዳይላሉ አልመሰላት አለ ። ከጥቂት ጊዜ ወዲህ ባሳያት ሁኔታ “ አውሬ ” እያለች ስታሰላስለው ነበርና በዚህ አዲስ መልኩ እርግጠኛውን አውሬ መሰሏት ፈራችው ። ማወደሻ ቃሉ ፥ በሙዚቃ ስልት ስሟን የሚጠራው ድምጹ ፥ ትህትናውና አሳቢነቱ ፥ መውደዱ የነጠፈበት ይህን ሁኔታ እየገረማት ውብሸትን ክፉኛ አስተዋለችው ።

የሳሎኑ በር ተንኳኳ ። ሁለቱም ወደ በሩ አስተዋሉ ። ኳኳታው ተደገመ ። የተጣደፈ ዓይነት ኳኳታ ስለነበረ ከትከሻዋ ዝቅ ብሎ ክንዶችዋን አጥብቆ እንደያዛት የኋሊት አራምዶ ከሶፋው ላይ አስቀምጧት በሩን ሊከፍት ተናዶ ሄደ ። “ ጤና ይስጥልኝ ፥ የመብራት ሂሣብ ” ብሎ ካርኒውን ገንዘብ ሰብሳቢው አቀበለው ። የሰፈሩ ሰው ዘጠና ከመቶው የመንግሥት ሠራተኞች በመሆናቸው ቅዳሜ ከሰዓት በኋላና እሁድ ብቻ ስለሚገኙ የመብራት ፥ የውሃና የስልክ ዋጋ ሰብሳቢዎች አካባቢውን የሚያዳርሱት በነዚሁ የእረፍት ቀናት ነው ።

መኝታ ክፍሉ ገብቶ የሚፈለግበትን ሂሣብ እስኪያመጣ አበባየሁ ያለቀሱ ዐይኖችዋን ፥ የጋሉ ጉንጮችዋን እየጠራረገች ጸጉሯን በጣቶችዋ እያመሰቃቀለች አሳምራ የነበረችበትን ሁኔታና ስሜት ለመደበቅ ፈጣን ማስተካከያ አደረገች ።

ብሩን ከፍሎ ፥ በሩን ዘግቶ ሲመለስ ፥ ፊቷን ቅጭም አድርጋ አስተያየቷን አክፍታ ከተቀመጠችበት ተነሳች ።

እንደገና ትክሻዋን ይዞ በፊቱ ላይ ባንሠራራ ፈገግታ በደመቁ ትናንሽ ዓይኖቹ ዐይኖችዋን ድርቅ ብሎ እየተመለከታቸው በሀሳብ ነጐደ ። አበባየሁም ገርሟት በትእግስት ጠበቀችው ። እሱ በአጐቱ ቤት ተጠግቶ ፣ እሷ በደብረ ብርሃን ከተማና በአካባቢው ነዋሪ በታወቁ ፣ በናጠጡ ቤተሰቦችዋና ቤተ ዘመዶችዋ መካከል ተንደላቃ ያሳለፉትን የት/ቤት የልጅነት ዕድሜና ለሷ የነበረውን ድብቅ ጉጉትና መውደድ ከነጭንቀቱ እንደገና አሰበው ። በማንኛውም ረገድ በነበራቸው ልዩነት ስትንቀው እንደነበረ ሲያስታውስ ቅሬታ ወጋው ። ሆኖም ምኞቱንና ፍላጐቱን እውን ለማድረግ ከባድ ጥረቱንና የሚገኝበትን ሁኔታና ደረጃ አይቶ እንደገና የኩራት ስሜት ወረረው ። ታላቅ ወንድሟ ቁምላቸው ትዝ አለው ። ሥልጣኑ ፣ ክብሩ ፣ ዝምድናውና ጥቅሙ በቅደም ተከተል ተገለጹለት ። ሌላውን ካናዳ ያለውን ወንድሟን አሰበው ። በቅርብ ባያውቀውም በዝምድናው ሳቢያ ጥቅም እንጂ ጉዳት እንደሌለው አመነ ። አባቷም ለሚኖሩባት የዱብረ ብርሃን ከተማ የልማት አውታሮችን እንደሚዘረጉ በልፈፋና በየግድግዳው በሚለጠፍ ደማቅ ጽሁፍ አሰምተው የፓርላማ ተመራጭ በመሆን ከአጼው የአስተዳደርና የመማክርት ክልል በመደባለቅ ጥቅምና ዝናቸውን ያካበቱ በመሆናቸው በረከታቸው የሚተርፍ መሆኑን ገመተ ። ሰፊውን የአበባየሁን ቤተሰብና ዘመድ አዝማዱን ሁሉ ለአፍታ ቃኘው ። በችግር በተሟሸው የልጅነት ሕይወቱ ይመኘውና ይቀናበት የነበረውን ይህን ቤተሰብ ሊደባለቅበት የተመቻቸ ሁኔታ ስለመጣለት ጉዳዩን ችላ ሊለው አልፈለገም ። ብቻ አንድ ስሜት እየከነከነ አስቸገረው ።

በአጐቱ ቤት ያሳለፈው የችግር የልጅነት ዕድሜውና በኋላም የኃይለማርያም ማሞ ት/ቤት የተማሪዎች በጐ

አድራጐት ድርጅት ያደረገለት ድጋፍ ለዩኒቨርሲቲ ትምህርት ወደ አዲስ አበባ ሲመጣ ተማሪዎች አዋጥተው የቋጠሩለት ስንቅና ያለበሱት ልብስ ከዛሬው ሕይወቱ ጋር ሊያስበው የማይፈልገውን የበታችነት ስሜት እየፈጠረበት አስጨነቀው ። ባለበት ክብርና ደረጃ እንደገና ሕይወቱን ከዚያች ከተማ ጋር ፣ ከዚያች ከተማ ነዋሪ ጋር ማያያዙን ጠላው ። ፊቱን ወደዚያች ያደገባት ከተማ አዞሮ ቢተኛ የሚያመው መስሎት የሚሰማው ውብሸት እንዳይላሉ ፈታኝ ሁኔታ ገጥሞት አበባየሁን እንደጨመደዳት በቆመበት በሀሳብ ሙግት ተንገላታ ። ዐይኖቹ በዐይኖቿ ላይ ቢያርፉም እያያት ሳያስተውላት በሷ ቤተሰብ ውስጥና በሱ ሁኔታ ውስጥ እየተመላለሰ ለረዥም ጊዜ ዝም አላት ።

“ ተማሪ ሆነህ የሚያውቅህ ሁሉ ዛሬም በደብረ ብርሃን እንደሀውልት ተተክሎ አይገኝ ፤ ቢገኝስ ታግሎ ከችግር መውጣት ቢያኮራ እንጂ አያሳፍር ፤ ይልቅ እድል አትግፋ ” የሚለው ሀሳቡ ሲያደፋፍረው ፤ ሌላኛው ደግሞ ‘ በሚያቆስል ትዝታና የበታችነት ስሜት ዘወትር መንፈስህን ከምትደነቁል ፤ ሰላማዊ ብቸኝነትህን ይዘህ እሷን ተዋት ” እያለው ፤ ለውሳኔ ተቸግሮ ዋለለ ። ዐይኖቹን ጨፈን አድርጐ ለቁርጥ ሀሳብ አንገቱን ደፋ አደረገና ቆየ። ባንኖ እና ደንግጦ እንደተነሳ ሰው እንደገና በፊቱ ላይ ፈገግታ እያነጠፈ ፤ “ ምን አልሽኝ” አላት ፤

“መቀለጃህ አይደለሁም ልቀቀኝ” ብላ በኃይል ልትመነጭቀው ሞከረች ። አያያዙ ስለ ጠበቀ ግን አልቻለችም ።

“ የበፊቱን ትክክለኛ ቃልና ሁኔታ መልስሽ ንገሪኝ”

“ ትርጉምም ስሜትም ሊሰጥህ አልቻለምና አልደግመውም ። ሀሊና ዬንም በማስተጋባው ቃል አልደነቁለው ም ። ልቀቀኝና ልሂድ ።”

" ምናለበት ደግመሽ ስትናገሪው ብሰማ "

" አልናገርም "

በቁጣ ጨምድዶ አርገፈገፋት ። ፈቷን ወደ ትከሻዋ መልሳ ዝም አለችው ።

" ንገሪኝ"

" ምኑን. "

" የመጀመሪያውን ቃል "

" ብትወድም ባትወድም አርግዣለሁ " አለችው ቀይ ፊትዋ ሳንባ እንደ መሰላ ።

ጐንበስ ብሎ ሆዷን ሳመው ። ቀና ብሎ ከንፈሮቿን ፈልቅቆ መጠጣቸው ። የዕንባዋ ትኩስነትና ጨዋማነት ተሰምቶታል ። በማግስቱ ለሚከበረው የእንቁጣጣሽ በዓል የገዛውን ውስኪ ከፍቶ በምሥራቹ መደሰቱን ገለጠላት ። የሚወለደውን ሕጻን በናፍቆት እንደሚጠብቀው ፤ በፍቅር እንደሚቀበለው ፤ በእንክብካቤ እንደሚያሳድገው አረጋገጠላት ።

አበባየሁም ሆነች ውብሸት እንዳይላሉ ከነበሩበት የሀሳብ ማዕበል ወጥተው በሚያስማማ አቅጣጫ ላይ በመድረሳቸው የመንፈስና የአካል እፎይታ አደረጉ። እንደገና ጐን ለጐን ተቀምጠው አንዱ የሌላውን የጋለ እጅ እየዳሰሱ ወደፊት ስለሚያደረገው የቀለበትና የሠርግ ድግስ ተወያዩ ። ቀለበቱና ሠርጉ በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ ለመልስ ጥሪ ወላጆችዋ ቤት ደብረ ብርሃን መሄዳቸውን ከንግግርዋ ተረዳ ። ድግሱ መቼ መደረግ እንዳለበት ግን በየበኩላቸው የሚሻለውን ቅርብ ጊዜ ረጋ ብለው እንዲያስቡበት ተስማሙ ። ሰከን ብላ በተጐነጩችው መጠጥና ቀደም ሲል በተሯሯጠባት ሀሳብና ጭንቀት የተነሣ ፊቷ እንደቀላ ቢቀርም

ሀሊናዋ ወደስተኋላ የሀሳብ ጭንቀቱን አውርዶ መረጋጋት ታየባት ። የጠነከረ ተስፋ ብትጨብጥም ሰውነቷ ደክሞና ተብረክርኮ ልፍስፍስ አለች ። በዚያ አጭር ጊዜ ውስጥ " እመቤቴ " ይላት የነበረው ወዳጅዋ " ወዲያውኑ አባባሉን ለውጦ " ባለቤቴ " እያለ ሲጠራት ሲያቆላምጣት ልዩ ስሜት ፈጠረባት ።

ይህንን ፍጹም የሆነ እፎይታ በማግኘቷ እጅግ ብትደሰትም በሴትነት ኩራትዋ ስሜቷን በመቆጣጠር ያልተደነቀች ፤ ያልተረበሸች መስላ ታየች ። ውብሸት እንዳይላሉ ሴትና ፍቅር ፤ ልጅና ትዳር ፤ ሰብአዊ ሞራልና ሰብአዊ ርኅራኄ ትርጉምና ጥቅማቸው ሲከሰቱለት የደረሰችው አበባየሁ እንባቸው በከንቱ ፈሶ ከቀሩት በርካታ ሴቶች የተለየችና ዕድለኛዋ ናት ።

የከሰዓት በኋላ የዋዜማ ሰዓታትን በጭንቅና ኋላም በእፎይታ አሳልፉ ፤ የማታ ማታ ወደ ቤትዋ ስትመለስ የኑሮዋን አቅጣጫ ቀይሳ ፤ ለወደፊት ግንኙነትዋ እልባት አኑራ ፤ ለመጽነስ አዲስ ባትሆንም ወልዶ ለመሣም ግን ሙሉ ተስፋ ጨብጣ ፤ ቤትና ትዳርዋን በምናብዋ እየተመላ ለሰችበት ከቅላቷ በላይ ፈክታ በአጋጊጥዋ ተሽቀርቅራ ነበር ። የእንቁጣጣሽን ዋዜማ በአንድነት እንዲያሳልፉ ቢጠይቃት ስላልተቀበለችው በማግስቱ ልትመጣ ወስነው ሸኛቷት ተለያዩ ።

ሣተና የሆነች ሠራተኛ ስላለችው ፤ የውብሸት እንደዳላሉ ቤት ዓመት በዓል ዓመት በዓል ሸቷል ። በተመላላሽነት ከሰዓት በኋላ እየመጣች የምትሠራላት ውዴ ቢበዛ የአስራ ስምንት አለዚያም የአስራ ስድስት ዓመት ለግላጋ ጠውላጋ ልጅ ብትሆን ነው ። ሁኔታዋ ከምንም ነገር አብልጦ ችግርዋን ይናገራል ። አንገተ ሰባራ ፤ አንደበተ ልስ

ልስ እግረ ፈጣንና ብሩህ አእምሮ ያላት ስለሆነች ውብሸት እንዳይላሉ በሥራዋ ሁሉ ይደሰታል ። ቤት ውስጥ የሚ ታጠቡ ልብሶቹንና ቤቱን እቃዎቹንም ጭምር በንጽህናና በጥንቃቄ ስለምትይዝለት ለረዥም ጊዜ እንድትሰራለት አድርጓል ። በዚህ ባለሙያነትዋና ጠባይዋ የመንደሯ ሰው ሁሉ የሚመርቃት የሚያደንቃት ልጅ ነች ። በተለይ ለትምህርትዋ ባላት ጥረት እንደ ምሳሌ በየቡናው ላይ ትጠቀሳለች ።

ሲሄድ እንደዋለ ፤ ጐምበስ ቀና ብሎ እንደደከመው ሁሉ ሰውነቱ ስለ ሸተተና ጠረኑ ስላስጠላው በቀዝቃዛ ውሃ ሊለቃለቅ ሲገባ ቁጠማ በስሱ በተን አድርጋ ነድ አጪሳ ጠላ በማቅረቢያ ሞልታ ፤ ራቱን ከጠረጴዛው ላይ በሥርዓት ሸፍና አቅርባ ቆየችው ። የቤቱ ጠረንና የተፈነጣ ጠቀው ቄጠማ አደይ አበባውም ደስ አለው ። ራሱን በፎጣ እያሻሸ የቤቱን ዙሪያ ተመለከተ ። ከቢፌው ላይ ያለው ሰዓት አንድ ሰዓት ከአምስት ደቂቃ ይላል ።

“ ውዴ” አላት እናቷ እንደሚጠሯት ፤ የውዴ ትክ ክለኛ ስሟ ግን ፍሬ መውደድ ቢሆንም ለአጠራር ስለሚ ረዝም በአጭሩ ውዴ ማለቱን ብዙዎቹ ይመርጡታል ። “ አቤት ” ከወጥ ቤት ብቅ አለች ። “ አውቶቡስ ታጫ ለሽ ሂጂ እቃውን እኔ አነሳሳዋለሁ ” እሺ ብላው ተሰና ብታ በጓሮ በር ወጥታ በድርሻ ቁልፏ በውጭ ቆልፋ ሮጠች የመጨረሻዋን ሃያ ሶስት ቁጥር አውቶቡስ አግኝታ ስድ ስት ኪሎ አፍንጮ በር አፋፉ ላይ ወርዳ ቁልቁል ወደ መን ደሯ ተፈተለከች ።

በጥልፍ የተንቆጠቆጠ ሸማ ለብሰው ገርዳሳ ሻሻ ቸውን ሸብ አድርገው ረጃጅም ባለ ብዙ ቀለም ጥለት መቀነታቸውን ታጥቀው በትክሻ እንቅስቃሴያቸው ፤ በወ

ገባቸው አሰባበቅ አጥንት የተፈጠረባቸው የማይመስሉ የአማራው ብሔረሰብ ተወዛዋዦችና አቀንቃኞች ፤ ከወገ ባቸው በታች እንደ እንዝርት የሚሾሩ የወላሞ ብሔረሰብ ዳንኪረተኞች ፤ አየር እየቀዘፉ የሚዋኙ የሚመስሉ የጉ ራጌ ሰዎች ፤ ሸማ ተሸፋፍነው የቁንዳላቸው መጨረሻ አብጦ ከትከሻቸው ላይ የተከመረና እንዲያው ሰበር ፤ እንዲያው ነካ ከሚያደርጉት ደካማ እስክስታ ጋር በሚ ሽከርከር አኳሄዳቸው ፈሰሰሰስ የሚሉ ፤ ከነሱ ይልቅ ከበ ሮአቸው የሚቅበጠበጥ የትግሬ ተወዛዋዦች እየተፈራረቁ የሚታዩበት የቴሌቢዥን ትርኢት ቤቱን ሞቅ አድርጎለ ታል ። ራቱን ከበላ በኋላ የቀረበለትን ወፍራም ጠላ እያ ጣጣመ የልጅቷን ሙያ እያደነቀ ጋቢውን በረዥሙ ተጐ ናጥፎ ተቀመጠ ። ከሳሎኑ ግድግዳዎች መጋጠሚያ መካ ከል ያለውን ባለ ቆብ ረጅም መብራት አብርቶ ደብዘዝ ባለው ወርቃማ ብርሃን ውስጥ ራሱን አዝናንቶ ከቴሌቭ ዢኑ ፊት ለፊት አንፈራጦ ተቀምጦ ነበር ።

አድርጐት አያውቅም ፤ በእንቁጣጣሽ ዋዜማ ብቻ ውን ተደምሞ ማምሸት ። ለራሱም ገረመው ። ወደ ቀኝ ዘወር ሲል ከሚያብረቀርቅ ጥቁር ማህጐኒ እንጨት የተ ሰራው ባለውድ ዋጋው ቢፌ በግርማ ሞገሱ አምሮ ታየው ወዲያው ልቡ ሌላ መጠጥ ከጀለና ጠላውን ትቶ የተጋመ ሰውን የውስኪ ጠርሙስ ከመለኪያ ጋር አቅርቦ መጠጣት ጀመረ ። ሁለቴ በርከት አድርጐ ከተጐነጨ በኋላ ውዝ ዋዜውን መመልከት ዜማውን ማዳመጥ ትቶ ቀስ በቀስ ህሊናው ወደ ጀመረው ጭውውት ተጐተተ ። የእለቱ ትር ኢት ከጅምሩ እስከ ፍጻሜው ወለል ብሎ ታየው ። አመ ጣጥዋን አቆነጃጀትዋን እንደገና በሀሳቡ አጤነው ። አበ ባየሁ እንደገና አበባ መስላ ታየችው ።

ድንገት በተቅለበለበ ድምጹ አስደነገጠው ። የቤቱ ሰላም ደፈረሰ ። ሀሳቡም ተቋረጠ ። የስልኩን መነጋገሪያ ከጎኑ አቅርቦ ጥሪውን ተቀበለ ።

" ሀሎ" . . .አቤት "

" አለሁልሽ "

" እንኳን አደረሰሽ ታዬ "

" እንኳን አብሮ በሰላም አደረሰን እመቤቴ "

" ላንቺ ቀርቶ ለሌላም ሰሚ ያስገርማል በዚህ ሰዓት በዚህ ዋዜማ ምሽት በቤቴ ውስጥ መገኘቴ አዲስ ነገር ነው ። ይኸውልሽ ዋዜማውን በቤቴ ውስጥ ጉድ ጉድ ስል ማሳለፌ ነው"

" ይገርምሻል ሳላስበው ዘመዶቼ ከገጠር መጥተው እንግዳ በእንግዳ ሆኛለሁ "

" እናቴና አጎቴ ናቸው "

" እንዴት ትቻቸው እመጣለሁ ፤ ታውቂያለሽ ሠራተኛዬ አዳሪ አይደለችም እሷ እንኳን ብትኖር ብቅ ብዬ አይቼሽ እመለስ ነበር "

" ታዬ ቅር አለሽ እንዴ "

" በጭራሽ ይኸንን ማሰብ የለብሽም እንዴት ከሀሳቤ ትወጫለሽ "

" ምናልባት ከሰዓት በኋላ ወደማታ ይወጡ ይሆናል ። ሌላው አጎቴ መጥቶ እንደሚወስዳቸው ደወሉ ነግሮኛል"

" አንቺም ቢሆን ዛሬ ማታና ነገ ቀን እንግዳሽ ብዙ ነው ። አጋጣሚውን መጠቀም አለብሽ ፤ ሥራም ያደክምሻል ስለዚህ ዘመዶቼን ሸኝቼ የማታ ማታ ብቅ እላለሁ "

" ለኔማ ብትመጪ ደስታውን አልችለውም ግን መድ ከምሽን አልፈልግሁትም "

" ከመጣሽም ወደ ማታ ነይ "

" ሴቶች ስትባሉ መጠራጠር ታበዛላችሁ ። ለሴላ

ሳይሆን አንቺን የማስተናግድበት ብቸኛ ጊዜ ለማግኘት ብዬ እንጂ ከፈለግሽ የእንቁጣጣሽ አበባ ይዘሽልኝ በጠዋት ድረሺ "

" እሺ ታዬ እመቤቴ የሰላም ዘመን ይሁንልሽ ላንቺም "

" አሜን ደህና እደሪ "

የሽሙጥና የፌዝ ሣቅ እየሣቀ ስልኩን ዘጋው ። እጆቹን አጣምሮ ለጭንቅላቱ አንተርሶ ወደ ሶፋው መደገፊያ እየተለጠጠ " እንግዲህ አባ ወራ መሆኔ ነው ፤በሞኖፖል ልያዝ እጄን ወድጄ ሰጥቻለሁ ፤ ታየች አባጨፍቅ ሰብሰብ በይ ወዳጄ " ብሎ ሣቁን ለቀቀው ። ብቻውን አውርቶ መሣቁ ለሱ ገረመው እንጂ ከሚያየው ውዝዋዜ ከሚመነጨው ድምጽ አምልጦ ለማንም የሚሰማ አልነበረም ።

ካቀረበው ዮሐንስ አራምዴ ውስኪ መላልሶ ተጎነጨና ሙቀት በደም ሥሩ እየጋለ መሠራጨት ሲጀምር በውጥን ወደ ተወው ሀሳቡ ተመለሰ ። ቃሉ በህሊናው ውስጥ አንቃጨለበት ። " አርግዣለሁ" የህሊናው ጆሮ ተቀባብሎ አደመጠው ። የዛሬው ቃል ለውሳኔ በመብቃቱ እንጂ ቃሉ በቃልነቱ አዲስ ሆኖ አላስደነቀውም ። ዛሬ በጺጋ ቢቀበለውም ደግሞ ደጋግሞ በተለያየ አቀራረብ የሰማውና የገፋው ቃል መሆኑን አመነ ።

ይህንኑ ቃል ፤ ፈራ ተባ ብለው በለሰለሰ አንደበት ወይም በድፍረት ፤ አለበለዚያም አሳስቀው ፤ አንዳንዶቹም አልቅሰው የነገሩትን ሴቶች ብዛት ቢያውቅም ብዙዎቹ ከነመልካቸው ከነስማቸው ጠፍተውታል ። አንዳንድ ለየት ባለ ሁኔታ ጨርሶ ያልዘነጋቸውን ሴቶችን አስታወሳቸው ገና የዩኒቨርሲቲ ትምህርቱን አጠናቆ ማዕረግ ያለው ሥራና ከፍ ያለ ደመወዝ ባገኘበት ዘመኑ ፣ አለባበሱ አነጋገሩ ፣ አካሄዱ አሳሳቁ ፣ እንደማግኔት ሴቶችን በዙሪያው ባሰባሰበበት ሰሞን ካወቃቸው ሴቶች መካከል አንዷ ተነጥላ ታየችው ።

በአበባየሁ አንደበት በጸጋ የተቀበለውን ቃል ያች ሴት ያኔም እያነባች እንደነገረችው አስታወሰ ። ቃል በቃል ያደረጉትን ምልልስ እንደገና በህሊናው ውስጥ አደመጠው።

" ውብሸት "

" ወዬ የኔ እመቤት "

" አንድ ነገር ልንገርህ "

" ንገሪኛ ፤ ድምጽሽን መስማት ጨዋታሽን ማዳመጥ ያረካኛል "

በመካከል ዝም ትላለች ።

" ንገሪኛ" ይላታል ለመስማት ጓጉቶ

" እሺ"

" ምነው ሀሳብ ወደ ኋላ ማሸሽ ጀመርሽ እንዴ ? እኔ እኮ ከኔ የሚደበቅ ምስጢር ይኖርሻል ብዬ አልገምትም "

" እሱስ ልክ ነህ አንተ የማታውቀው ነገር የለም እንድታውቀውም ያስፈልጋል "

" እኮ ምንድነው ነገሩ"

" ልናገረው ፈራሁ "

" አቦ ንገሪኝ ማድረግ የምችለውን ሁሉ ላንቺ ለማድረግ ዝግጁ ነኝ"

" አርግዣለሁ "

" ምን"

" አርግዣለሁ አልኩህ "

" አትጨማለቂ እንዲህ ዓይነቱን የደካሞች ዘዴ በኔ ላይ መሞከር አያዋጣሽም "

" ተው እንጂ ሌላው ቀርቶ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት የተናገርከው ቃል ያንቅህል "

" እንዲያውም በቃኝ ካንቺ ጋር ያለኝን ግንኙነት አልፈልገውም ። አረገዝኩ ወለድኩ የሚል ጭቅጭቅ መስማት አልፈልግም ። ግንኙነታችን ካሁን ጀምሮ ተቋርጧል ። ምናልባት እንድመክርሽ ከፈለግሽ አረገዝኩት የምትይውን አውጥተሽ ጣይው "

" ከመቅጽበት እንዴት ትለወጣለህ ወደድኩሽ ስትለኝ ኖረህ የምችለውን ላደርግልሽ ዝግጁ ነኝ ስትለኝ የነበርክ ሰው ፣ እንዴት እንዲህ በጥላቻ ታመናጭቀኛለህ "

" በቃኝ አልፈልግሽም ። ስለ እውነት ከሆነ ዱሮውንም ካንቺ ፍቅር አልነበረኝም ። "

" አስብሻለሁ ፣ አሰላስልሻለሁ ፣ ያለሽበት ሥፍራ ቢርቅም ልረሳሽ ቀርቶ ለሰኮንድ ከህሊናዬ አላወጣ

ሽም እያልክ ስታላዝን የነበረው ከኔ የምትፈልገውን ጥቅም እስክትነክስ ነበራ ”

“ ያ በዚያ ሰዓት የተሰማኝ ያለፈ ነገር ነው ”

“ ውትወታህና ማስመሰልህ ጠልፎ እስኪጥለኝ ድረስ ምን ያህል ወድቀህ እንደ ተነሣህ አትረሣምና ያን ያህል ራሴን ያከበርኩ መሆኔን እወቅ ። ታምኜ እምነት ባለማጉደሌ ደስ ይለኛል ። የማትታመን ርካሽ በመሆንህ ግን ንቄሀለሁ ”

“ ግትርና ግድርድር ስለ ነበርሽ ለማስተማር ያደረግሁት ጥረት ሁሉ ከፍቅር ተቆጥሮ ኮሆነ ተሳስተሻል ። በግልጽ አነጋገር ከአጉል ባህሪሽ ለማቃናት ያደረግሁት ማስተካከል ነበር ”

“ እኔን ሳይሆን የምታታልለው ራስህን ነው ። ኩሩና ቁጡብ መሆንሽ የሴትነት ጥንካሬሽ ያኮራኛል ፤ ባንቺ ላይ ያለኝን እምነት ከፍ ያደርገዋል ፤ እያልክ ስትመጻደቅ አልነበረም ? እንዴት ዛሬ አጉል ባህሪ ሆኖ ታየህ ”

“ ነገርኩሽ እሱ ያለፈ የተረሣ ጉዳይ ነው ። ከዚህ በኋላ ትዝታ እየጐተተሽ እንድትጨቀጭቂኝ አልፈልግም ። ይልቅስ ለራስሽ ስትይ አረገዝኩ የምትይውን አውጥተሽ ጣይው ”

“ አልችልም ”

“ እንዴት አትችይም ”

“ ይህ አንተን የሚመለከት አይደለም የግል ወሳኔዩን ይጠብቃል ”

“ እና በዚህ ሰበብ ልትጣበቂብኝ ፈለግሽ፣እንዳይመስልሽ ከዚህ በኋላ ይህን በተመለከተ ስሜን ብትጠሪው ወደ ከፋ ደረጃ እንሸጋገራለን ።

ሃምሣ ብር ከደረት ኪሱ አውጥቶ እንደወረወረላት በትክክል ትዝ አለው ፡

“ ምንድነው ” ስትለው

“ ለችግርሽ መርዳቴ ነው አስወጭበት ” ይላታል

ታዲያ ሴቲቱ የሴት ነገር ሆኖ እንባዋ ቢወርድም፣ ቅስሟ ቢሰበርም ፣ የመንፈስ ጥንካሬ የተመረኮዘች ስለነበረች ልብሷ ላይ የወረወረውን ባለ ሃምሣ ብር ኖት ጨባብጣ ወርውራ ረጅም አፍንጫውን እንደመታችው አስታወሰ።

ከዚያም በኋላ የተጠላው ጽንስ ዕድገቱን አከናውኖ መወለዱን የወሬ ወሬ ከሰዎች መስማቱንና ከብዙ ጊዜም በኋላ ስለ ማሳከሚያ እርዳታ ጥያቄ አንድ ጊዜ ብቻ ከሴትዩዋ ጋር መነጋገሩ ቁልጭ ብሎ ታየው ። “ ሺት” አለ። ትዝታውን ይሁን አድራጐቱን በመጠየፍ ። ይኸኔ ከፊቱ ያለውን የተቀዳ ውስኪ ጠብታ ሳያስተርፍ ተንጋሎ ጨለጠው ። እንዲያውም የትውስታው መጠን ጨመረበት። የትዝታው ወሰን ሰፋና አንድ ነገር ብልጭ አለለት ።አስፈላጊ መረጃዎች የሚላቸውን አሰባስቦ ተጠንቅቆ ከሚያስቀምጥበት ማኅደር መካከል ትኖራለች ያላትን ወረቀት ፍለጋ ወደ መኝታ ክፍሉ ገባ ።

በርካታ ወረቀቶች የሚገኙበትን ማኅደር ይዞ ተመልሶ ከነበረበት ሶፍራ ተቀምጦ ማገላበጥ ጀመረ ። ከብዙ ዓመታት በፊት ያስቀመጣትን የታጠፈች የሀኪም ማዘዣ ወረቀት አገኛት ። እግረ መንገዱን በማስታወስ ችሎታ

ው ራሱን አደነቀ ። ወደ መቀመጫው መደገፊያ መለስ ብሎ ተደግፎ ያችኑ ወረቀት ልብ ብሎ ተመለከታት ። ቅጥልጥሉን የዶክተር ጽሁፍ አንብቦ ባይረዳውም መልሶ መላልሶ በዐይኖቹ ቃኛት ። የታዘዘውን መድኃኒት ምንነት ሊያውቅ ባለመቻሉ በወረቀትዋ ላይ እንዳፈጠጠ ባለ ጉዳይ የነበረችው ሕጻን በሕይወት መኖርዋን ወይም በወጋት ሕመም በሞት መሰለቧን አሰላሰለው ። የልጅቷንም ጾታ ያወቀው በወረቀቱ ላይ የተጻፈውን መግለጫ አንብቦ ነበር ።

የያዛትን ትንሽ የሐኪም መድኃኒት ማዘዣ ወረቀት እያየ ወደ ሌላ ትዝታ ተሸጋገረ ። አብሮት በዩኒቨርሲቲ የተማረውንና ለረዥም ዘመን የልብ ጓደኛው የነበረውንም ሰው አወሳው ። የያዛትን የሐኪም ወረቀት ከሴትዬዋ ተቀብሎ ለሁለተኛ ጊዜ ያመጣለት እሱ ነበር ። ጓደኛው አድራጎቱን በመቃወም በሰብአዊ ርኅራሄ ስሜት ማንም ማድረግ የሚችለውን እርዳታ ባለ ጉዳይ መሆኑን በመካድ ባለ መሰንዘሩ አጥላልቶ እንደሰደበውና በዚህም ተደባድበው የሱ ጥርሱ ሲሸረፍ ጓደኛው የግንባር ፍንክትና ጠባሳ ማትረፉን ተገነዘበ ። ያኔ ጠፋች ብሎ የሸሸጋትን ወረቀት እያገላበጠ አድራጎቱን ጠላው ። ወረቀቷን መሸሸጉ ፤ በፀና ሕመም የተለከፈችው ሕፃን በሥቃይ ላይ እንዳለች ስለሰማና ፤ ለብዙ ወራት ያስታመመቻት እናቷ እጅ እንዳጠራት በማወቁ በለጋ እድሜዋ እንድትሞትና የመድኃኒት እርዳታ እንዳይደርስላት ለማደናቀፍ አስቦ ሆን ብሎ ያደረገው መሆኑን ሲያስታውስ ዘገነነው። ፀፀት ቢጤም ተሰማው ።

ከመቼውም በዚያን ሰዓት ህሊናው በቀና እይታ ያችን ሕጻን ተመለኮታት ። ሊፈልጋትም ተነሣ ። “ የት ትሆን” አለ በጐረነነ ድምፁ ። በእርግጥም ከዚያ በኋላ

በሥራ ምክንያት ከአገር አገር ሲዘዋወር ከመ/ ቤት ወደ መ/ቤት ሲቀያየር በአጋጣሚ እንኳን ሴትዬይቱን ወይም ያንን ጓደኛውን አይቶዋቸው አያውቅም ። ይህን በተመለከተ ዳግም የሰማው ጉዳይም አልነበረም ። ነገሩ ሊከነክነው ጀመረ ።

“ የት ደረሱ ” አለ ትዝታው ከፊቱ የደቀናቸውን ጓደኛውን ፤ ሕፃንዋንና እናቲቱን ተራ በተራ እየተመለከታቸው ።

ክብረ ህሊናዋን አዋርዶ ፤የስሜቱና የፍላጐቱ ውጥረት ሲረግብ የተፋትን ሴት ቁመናዋን ፤ መልኳን ፤ ቀረቤታዋን በግልጽ ለመመልከት እያሰበ ፤ በየዋህነትዋ ያተረፈችውን ችግርና ውርደት መዝኖ እንደማዘን ቃጣው ።

እንደገናም በወንደላጤነት ሕይወቱ ያወቃችውን ሴቶች ሁሉ ተራ በተራ ለማስታወስ እየሞከረ በሴትነት ባህሪ ላይ ያለው ትዝብት አንሠራራ ። “ መጥኔ” አለ ድምጽ አውጥቶ ። “ መጥኔ ፤ ሴቶች ሲባሉ ፍቅር የሚሉት ሞኛ ሞኝ ጨዋታ እየገመተተ ገደል የሚከታቸው ከብቶች፤ አንዷ በሌላዋ ችግር የማትቀጣ ፤ በአፍአዊ ፍቅር በተስፋ ስጦታ የሚደለሉ ገብሶች ፤ አርቆ ማስተዋል ፤ ጠርጥሮ መመራመር የሚጐላቸው ግልቦች ፤ እውነትም ልባቸው ከከንፈራቸው ጫፍ የተንጠለጠለ ነው የሚባለው ሀቅ ነው ። ምናልባትም ህሊናቸው ከጡታቸው ራስ የተጣበቀ ሳይሆን አይቀርም ። ወይድኩሽ ባሏት ሰሞን ሳታስተውል ትከንፋለች ። ከችግር እየሰመጠች ሕይወቷን ስታጨልመው ፤ የእድል ቀንዲልዋን ስታጠቁረው ትገለፍጣለች። የኋላ ኋላ ከእውነተኛው ሁኔታ ተዘፍቃ ስትነቃ የመረረ ልቅሶ ትንፋረቃለች ። ሺት ” አለ ። ለሴቶች ያለውን ግምትና ንቀት ከተነተነው በኋላ ። ወንድ ሆኖ በመፈጠ

ሩም ደስ አለው ። ሆኖም ሴቷቱንና ሕፃኗን በዓይነ ህሊናው ከወዲያ ወዲህ መፈላለጉን አልተወም ። በተለያዩ የኑሮ ዘይቤ ስሎ በውስጡ ቀረጻቸው ። የታየው የምኞቱና የምናቡ ነፀብራቅ እንጂ እርግጠኛው ሕልውናቸው አልተከሰተለትም ። ትኩረቱ የጠነከረው በሕፃኗ ላይ ነበርና " የት ትሆን " አለ ዳግመኛ ። ከርዳዳ ፀጉሩን እያሻሸ የራሱን ጥያቄ ራሱ መለሰውና የያዛትን ወረቀት እንደገና አጣጥፎ አስቀመጣት ። በገጸ ምድር ወይም በከርሠ ምድር ትኖራለች ብሎ ደመደመ ።

ቀስ በቀስ እየተቀጣጠለና እየነደደ እየበራ በአእምሮው ውስጥ የሞላው ሀሳብ ሊለቀው አልቻለም ። ሰውነቱ በፈጠረው ግለት ወርዝቷል ። " እሱስ ቢሆን የት አባቱ ደረሰ " አለ ጓደኛውን የያኔ ትክክለኛነቱ ገና በዚያ ሰዓት ተከስቶለት ። ሽራፉ ጥርሱን እየዳበሰ ጓደኛውን በመውደድ ስሜት አሰበው።ያሳለፏቸውን የአንድነት የመግባባት ወቅቶች በፈጣን ትውስታ ቃኛቸው ። የኋላ ኋላ የሌሊቱ ጊዜም በመዘቃዘቁ ፤ በመጠጡም ሆነ በእንቅልፍ ጫና ቀስ በቀስ በመድከሙ ትዝታ ማመንዠኩም ስለ ሰለቸው ፤ ከመለኪያው ውስጥ የተረፈውን መጠጥ ጨልጦ ቴሌቪዥኑን ዘግቶ መብራቱን አጥፍቶ ወደ መኝታ ክፍሉ ገባ ።

ዘመን በዘመን መለወጡን የሚያበስረው የመድፍ ድምጽ ንጋቱ ላይ ከእንቅልፉ ቀሰቀሰው ። እንደ ተንጋለለ እየተደጋገመ የሚያስገመግመውን የመድፍ ተኩስ ይቆጥር ጀመር ። በመሀል ሰለቸውና አቋረጠው ። ከመድፉ ድምፅ በኋላ በአካባቢው ያሉ ሰዎች ድምፅና የበጐች ፤ የዶሮዎች ፥ ጩኸት ተሰማው ።

" የእንቁጣጣሽ ማለዳ ፤ የአዲስ ተስፋ ብርሃን በየሰው ልብ የሚያቆጠቁጥበት ጠዋት ፤ የደላውም የሚፎ

ክተውም ለመኖር ተጨማሪ ሕይወት ለመቀጠል የሚመኝበት ፤ የሚሳልበት የአዲስ ዘመን መባቻ ፤ አለ በጀርባው ተንጋሎ እንደተኛ ለእንቁጣጣሽ የሰጣትን መግለጫና ትንታኔ እየደረደረ ። ቀጠል አድርጐም በአዌው የአገዛዝ ሥርዓት ላይ ያለው ጥላቻ እያንሠራራበት እንቁጣጣሽን ተጨማሪ መግለጫ ሊሰጣት ወደደ ።

" እንቁጣጣሽ ፤ የሠመረለት ትፍስህትና በረከቱን የሚለካብሽ ሚዛን ፤ የጠመመበት ደግሞ የረድኤት መና ጠብታ ማጣቱን የሚታዘብብሽ ቆይታ ፤ ያለው ባለው ላይ ሊጨምር ፤ ሥልጣን ኮርቻ ላይ የተቆናጠጠ በዘር ማንዘሩ በአልጋ ወራሽ በቢትወደዱ ጥፍሩን አስልቶ አጨባበጡን አጠንክሮ ላለመነቃነቅ ይበልጥ ሊጣበቅ ፤ የወደደ ፍቅር ሊጐነጭ ፤ ያገባ ሊወልድ ሊከብድ ፤ የታመመ ሊድን ፤ የሚማር ውጤቱ ሊሰምርለት ፤ የደዌ ቁራኛውም ሰላማዊ ሞቱን የሚናፍቅብሽ ፤ ውጥንቅጥ ምኞት ውጥንቅጥ ስለት ፤ ውጥንቅጥ ቃል ኪዳን የሚፈስብሽ ቀን አይ እንቁጣጣሽ አንቺ አታልፊ አዚማም አዙሪት ፤ ትውልድ እንደ ጐርፍ ያልፍብሻል ። እንቁጣጣሽ አልፈሽ ደሞ ሌላዋ እንቁጣጣሽ ስትተኪ የእድሜውን መጐረድ ሳይረዳ የሰው ልጅ በተስፋ የሚያጐበድድብሽ መተተኛ ቀን ፤ አይ እንቁጣጣሽ አለና በአልጋው ውስጥ ተወራጨ። ለእንቁጣጣሽ በሰጣት ስያሜና መግለጫ በርካታ ሁኔታዎችን እያገናዘበ ቅንጣት የተግባር ጭብጦ ሊያቀርብ ቢጣየቅ ማቅረብ የማይችል የራሱ ገመና ባዶነት ተሰማውና " ምን አገባኝ አቦ የፈለገችውን ትሁን " ብሎ ሀሳቡን ገታ ። እንደገና ጆሮውን ለአካባቢው ድምፅ ሰጠ ።

በዚያ ማለዳ በዚያ ውርጫማ ጠዋት ለ ' አበባየሁ ሆይ " ጭፋሮ የተሰናዱ ልጆች ከበሮአቸውን ሲያሟሹ